# አርሊንግተን ካውንቲ

## የልጆች እንክብካቤ/ማቆያ እና የጥራት ደረጃ ማሻሻያ የሚሆን

## የገንዘብ አቅርቦት ማስታወቂያ

## ኦክቶበር 30 ቀን፣ 2024 ዓ.ም

### ማጠቃለያ እና መግቢያ

የChild Care Initiative [ቻይልድ ኬር ኢንሼቴቭ] (CCI) ለአርሊንግተን ቤተሰቦች የልጆች እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎቶችን ማቅረብ ላይ ያሉትን ተግዳሮቶች ለመፍታት የተዘጋጀ ስትራቴጂካዊ መዋቅር አቅርቧል። CCI ሶስት ነገሮች ላይ ያተኩራል፦

- *ተደራሽነት* – ለህዝብ ድጎማ ሴፍቲ ኔት ፕሮግራሞች ላይ የተቀመጡትን መስፈርቶች ውስጥ የተቀመጠውን የገቢ መጠን ለሚያሟሉ ቤተሰቦች ላይበልዩ ሁኔታ የሚያተኩር፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የ፡ የልጆች እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ።
- *ተገኝነት* – የልጆች እንክብካቤ/ማቆያ ክፍት ቦታዎችን የማግኘት እና የመጠቀም ሁኔታን ማሳደግ።
- *ጥራት* – የሁሉንም የልጆች እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎቶችን ደህንነት እና ጥራት ማጎልበት።

2017-2018 ዓ.ም ውስጥ ከተዘጋጀ ጀምሮ፣ CCI እነዚህ ግቦች ላይ የሚታዩ መሻሻሎችን አምጥቷል። ኤፕሪል 2024 ዓ.ም ላይ፣ በአርሊንግተን ውስጥ የሚታወቁ የልጆች እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎች ቁጥር 8,884 ነበር – ይሄም ዕድሚያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ 69% የሚሆኑትን የካውንቲውን ሕፃናቶች ለማገልገል በቂ ነው፣ ይሄ ቁጥር ከ 2017 ጋር ሲነፃጸር በ 51% ጨምሯል። በተጨማሪም፣ ከኤፕሪል 2024 ዓ.ም ጀምሮ፣ በአርሊንግተን የልጆች እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎት መስጫ ክፍት ቦታዎች ውስጥ 51% የሚሆኑት እውቅና የተሰጣቸው ወይም በጥራት ደረጃ የሚሰሩ የልጆች እንክብክቤ/ማቆያ አገልግሎት ማዕከሎች ወይም የቤተሰብ የልጆች እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ነበሩ – ይሄ ቁጥር ከ 2017 ጋር ሲነፃጸር በ 13% ጨምሯል።

### አሳብ እና ዓላማዎች

ICCIን በመደገፍ፣ የካውንቲው ቦርድ *የአንድ-ጊዜ* ብቻ የሚሰጥ $5 ሚሊዮን በጀት መድቧል። $4,435,420 ሚሊዮን የሚሆነው ከዚህ ቀድሞ ወጥቶ የነበረው የገንዘብ አቅርቦት እንዳለ ማስታወቂያ [Notice of Funding Availability] (NOFA) አካል ሲሆን አዲስ ተመጣጣኝ ዋጋ የሚያስከፍሉ የልጅ እንክብካቤ/ማቆያ ክፍት ቦታዎችን ለመፍጠር የካፒታል ወጪዎች ላይ ድጋፍ ለመስጠት ይውላል። ቀሪው $564,580 ደግሞ የዚህ NOFA አካል ይሆናል፣ በዚህም መሰረት *ጥራቱን የጠበቀ የልጆች እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎት ፕሮግራሞችን በመፍጠር፣ በማስፋፋት እና/ወይም በማሻሻል በአርሊንግተን ካውንቲ ውስጥ ጥራቱን የጠበቀ የልጆች እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ለማገዝ ፕሮፖዛሎችን ለመቀበል ይውላል።*

ካውንቲው የሚቀርቡት ፕሮፖዛሎች ከኣነዚህ ሁለት ምድቦች ውስጥ እንደሚሆኑ ያምናል – አቅም ግንባታ ወይም የጥራት ደረጃ ማሻሻል – እና የፕሮፖዛሎች አብነት ሊያካትት የሚችለው የሚከተሉትን ሲሆን ነገር ግን በእነዚህ ላይ ብቻ አይወሰንም፦

- የአቅም ግንባታ
    - የልጆች እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎት ሰጪ ፕሮግራምን ለመጀመር ወይም ለማስፋፋት የሚያግዝ የስራ ተቆራጭ ባለሙያ (ለምሳሌ፣ የገበያ ፍላጎት ትንታኔ፣ የቦታ አመራረጥ፣ የፕሮጀክት ዕቅድ፣ የገንዘብ ትንታኔ፣ ንድፍ እና ግንባታ፣ የሰራተኛ ቅጥር ወዘተ)
    - የስራ ሂደቶችን ክንውን የሚያዘጋጁ እና የሚተገብሩ በስራ ተቋራጭነትን የሚሰሩ ባለሙያዎች (ለምሳሌ መመሪያዎችን፣ ማረጋገጫ ዝርዝሮችን፣ ፖሊሲዎችን፣ የስራ ሂደቶችን፣ የድንገተኛ ጊዜ ዕቅዶችን ወዘተ)
    - የሙያ ልማት
- የጥራት ማሻሻያ
    - የካሪኩለም ወይም የምዘና መሳሪያዎች
    - ምስክር ወረቀቶች/ሰርተፊኬቶችን ማግኘት
    - ለዕድሜ የሚመጥኑ መፃህፍትን እና መጫዎቻዎችን ማዘጋጀት
    - የመማሪያ ክፍሎች ወይም አቅርቦቶች
    - ጤና እና ደህንነትን የሚደግፉ ዕቃዎች

የዚህ የገንዘብ አቅርቦት ባህሪ አንድ ጊዜ ብቻ የሚሰጥ ስለሆነ፣ አገልግሎት ሰጪዎች ልክ እንደ የሰራተኛ ደሞዝ እና ጥቅማጥቅሞች ለመሳሰሉ ከፍተኛ ወጪዎች ፕሮፖዛሎችን ማቅረብ የለባቸውም።

## የፕሮፖዛል አቀራረብ መስፈርቶች

ለገንዘብ አቅርቦቱ ማንኛውም ዓይነት የልጅ እንክብካቤ//ማቆያ አገልግሎት ሰጪዎች ፕሮፖዛሉን ማስገባት ይችላሉ። ምንም እንኳን አንድ ተቋም ከአንድ በላይ ፕሮፖዛል ያስገባ፣ በሁለቱም የገንዘብ አቅርቦት ምድቦች ላይ የገንዘብ/ፈንድ ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም፣ ወይም ለብዙ ነገሮች የፈንድ ጥያቄ ያቀረበ ቢሆንም – ለማንኛውም አንድ ተቋም የሚሰጠው የገንዘብ መጠን ከ $75,000 በላይ ላይበልጥ ይችላል።

የሚቀርበው ፕሮፖዛል 12-ነጥብ ታይምስ ኒው ሮማን ፊደል በሲንግል-ስፔስ የተፃፈ መሆን አለበት ነገር ግን ከ 7 ገጽ በላይ መብለጥ የለበትም። እባክዎን በፕሮፖዛሉ ውስጥ የሚከተሉትን መረጃዎች እንዲካተቱ ያድርጉ።

1. **የማመልከቻ ደብዳቤ።** የማመልከቻው ደብዳቤ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦

    ሀ. የአመልካች/የድርጅቱን ስም፣ አድራሻ እና ዋና ስልክ ቁጥር

    ለ. የአመልካቹ የህግ ሁኔታ አጭር ማብራሪያ፣ ለምሳሌ 501(c)(3)፣ LLC፣ ሌላ። (እባክዎን የዚህ ክፍል መጨረሻ

    ላይ የተጠቀሰውን የሚያስፈልጉ ሰነዶች ዝርዝር ተመልከቱ።)

    ሐ. ስም፣ ርእስ፣ ኢሜይል አድራሻ፣ እና የማመልከቻው ደብዳቤ ላይ የሚፈርመው ቀዳሚ ሰው ስልክ ቁጥር እና

    በማንኛውም ስምምነት ላይ ፈራሚውን አመልካቹን በህግ ማሰር እንደሚችል የሚያረጋግጥ መግለጫ

2. **መግቢያ።** ከዚህ ቀደም የነበሩትን ወይም ሊቋቋሙ የታሰቡትን የልጆች እንክብካቤ/ማቆያ ፕሮግራሞችን የሚከተሉትን በመጥቀስ ይግለጹ፦

ሀ. ያሉት አጠቃላይ የልጅ እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ቁጥር እና በልጅ እንክብካቤ/ማቆያ

አገልግሎት ሰጪ ድርጁቱ አገልግሎቱን የሚያገኙት ህፃናት የዕድሜ ክልል መግለጫ

ለ. የልጅ እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ የሚገኝበት ቦታ አድራሻ

ሐ. የስራ ቀናት/ሰዓታት – ለምሳሌ ልክ እንደ ቅዳሜና እሁድ፣ ምሽት፣ ለሊት ሙሉ የመሳሰሉ ያልተመለዱ የስራ

ሰዓታት ላይ የልጅ እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቱ ክፍት ነው?

መ. በአሁኑ ሰዓት ያሉ ወይም ለወደፊቱ የሚጠበቁ እውቅናዎች፣ ድጋፎች እና/ወይም የተገኙ ወይም የሚከተሉት

የጥራት ደረጃዎችን

3. **ጥራት።** ለወደፊቱ የሚተገበር ወይም በአሁኑ ሰዓት ላይ ያለ ፕሮግራም ውስጥ ጥራት ላይ ያላቹህን አካሄድ ግለጹ፡-

ሀ. የልጆችን አካላዊ፣ አእምሮዓዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ደህንነት እና ዕድገትን እንዴት ያሳድጋሉ?

ለ. ቀኑን ሙሉ ልጆች ለዕድሚያቸው የሚመጥኑ ተግባራት ላይ እንደሚሳተፍ በምን ታረጋግጣላቹህ?

ሐ. ለልጆቹ እና ለቤተሰቦቻቸው በከፍተኛ ደረጃ ጥራቱን የጠበቀ የልጅ እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎት ለመስጠት

ሰራተኞቻቹሁን እንዴት ታሰለጥናላቹህ እና በሙያ ታሳድጋላቹህ?

4. **ፕሮፖዛሉ።** የፕሮጀክታቹሁን ዝርዝር ማብራሪያ ግለጹ፣ ይሄ የሚያካትተው፡-

ሀ. ፕሮጀክታቹህ የሚሞላው ክፍተት ወይም ፍላጎት።

ለ. የልጅዎን የልጅ እንክብካቤ/ማቆያ አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ደረጃን እንዴት የእርስዎ ፕሮጀክት እንደሚያሻሽል

ማብራሪያ መስጠት

ሐ. የፕሮጀክቱ በጀት

መ. የፕሮጀክቱ የጊዜ ሰሌዳ

ሠ. ከዚህ ፕሮጀክት ጋር የሚያያዝ ቀጣይነት ያለው የሚያወጡት ወጪ አለዎት? ያ ከሆነ፣ እነዚህን ወጪዎች እንዴት

ይሸፍናሉ። ያስታውሱ ይሄ NOFA የሚሰጠው አንድ ጊዜ ብቻ ነው።

5. **ፍትሃዊነት።** ለወደፊቱ የሚተገበር ወይም በአሁኑ ሰዓት ላይ ያለ ፕሮግራም ውስጥ ፍትሃዊነት ላይ ያላቹህን አካሄድ ግለጹ፡-

ሀ. በአርሊንግተን ካወንቲ ውስጥ የእርስዎ ፕሮጀክት እንዴት በልጆች መካከል ያለውን ኢፍትሃዊነት ችግር ይፈታል?

ለ. የእርስዎ ፕሮግራም ለሰራተኞች፣ ለልጆች እና ለቤተሰቦች አካታች የሆነ ከባቢን እንዴት ይፈጥራል (ወይም ሊፈጥር

ይችላል፣ ፕሮግራሙ እስካሁን ድረስ ተግባር ላይ ካልዋለ)?

6. የእሱ ፕሮፖዛል ግምገም ላይ ካውንቲው ማጤን የሚገባው አመልካቹ ተዛማጅ ነው በማለት የሚያስባቸው ማንኛውም ሌሎች መረጃዎች።

ሌሎች ፕሮፕዛሉ ውስጥ መጠቀስ ያለባቸው ነጥቦች፡-

- ሁሉም ፕሮግራሞች ሁሉንም ተግባራዊ የሚደረጉ የግዛቱ እና የአካባቢውን የስራ ፈቃድ የማውጣት መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው።
- ካውንቲው ለትርፍ ከተቋቋሙ እና ለትርፍ ካልተቋቋሙ አጋር ድርጅቶች ፕሮፖዛሉን ይቀበላል፡-
    - ሁለቱም ለትርፍ የተቋቋሙ እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ አመልካቾች ህጋዊ የንግድ ፈቃዳቸውን ማቅረብ እና በገቢዎች ኮሚሽነር ቢሮ ውስጥ ባለው ያልተከፈለ የንግድ ፈቃድ ታክስ ወይም የግብር ዕዳ የሌላቸው መሆን አለባቸው። ይሄ ሰነድ የ 7-ገጽ ገደብ ውስጥ አብሮ አይቆጠርም።
    - ለትርፍ-ያልተቋቋሙ አመልካቾች ለትርፍ-ያልተቋቋሙበትን ሁኔታ የሚያሳይ ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው። ይሄ ሰነድ የ 7-ገጽ ገደብ ውስጥ አብሮ አይቆጠርም። ለትርፍ-ያልተቋቋሙበትን ሁኔታን ለማሳየት ከሚከተሉት ማንኛውም ሰነዶች ውስጥ ካቀረቡ ለማስረጃነት ተቀባይነት ይኖረዋል፡-
        - በIRS ህገ ደንብ ክፍል 501(c)(3) ውስጥ በጣም የቅርብ ከግብር ነፃ የሚሆኑ ድርጅቶች ዝርዝር ውስጥ በኢንተርናል ሬቬኑ ሰርቪስስ (IRS) ውስጥ የአመልካቹ ድርጅት ዝርዝር ውስጥ እንዳለ የሚያሳይ ማስረጃ
        - የአሁኑ ከIRS ገቢ ግብር ከመክፈል ነፃ የተደረጉበት ሰርተፊኬት
        - ከግዛቱ ግብር ሰብሳቢ ባለስልጣን፣ ከግዛቱ አቃቤ ህግ፣ ወይም ሌሎች ተገቢ የግዛቱ ባለስልጣናት በኩል አመልካቹ ድርጅት ለትርፍ-ያልተቋቋመ እንደሆነ የሚገልጽ እና የሚገኘው የድርጅቱ ትርፍ ለማንኛውም የግል አክሲዮን ባለድርሻ ወይም ግለሰቦች እንደማይከፈል የሚያሳይ መግለጫ።
        - የድርጅቱን ለትርፍ-ያልተቋቋመ ሁኔታን በግልጽ የሚያሳይ ድርጅቱ የተቋቋመበትን ሰርተፊኬት አፍ ኢንኮፖሬሽን ሰነድ ወይም ተመሳሳይ ሰነድ ምስክር ወረቀት ኮፒውን
        - ከላይ የተጠቀሱትን ማረጋገጫ ሰነዶች በግዛቱ ወይም በብሔራዊ ወላጅ ድርጅት ከተሰጡ እና አመልካቹ ድርጅት ለትርፍ-ያልተቋቋመ አጋር ድርጅት እንደሆነ የሚያሳይ የተፈረመበት መግለጫ በወላጅ ድርጅቱ ከቀረበ
- ሁሉም አመልካቾች ለታቀደው ፕሮጀክት ማንኛውም አስፈላጊ የሆኑ ከመንግስት ተቋማት የሚሰጡ ፈቃዶችን የማግኘት ሃላፊነት አለባቸው።

- ለሽልማቱ የሚመረጡ ከሆነ፣ የሽልማቱ አሸናፊ ድርጅቶች የሚከተሉን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፦
    - የ W-9 ቅጽ ማቅረብ እና የክፍያ መቀበያ መመሪያዎችን ማረጋገጥ።
    - ፕሮጀክቱ እንደተጠናቀቀ ለማሳየት አንድ ወይም ከዛ በላይ ሪፖርቶችን የማቅረብ።
    - ድርድር የሚደረግበትን እና ተግባር ላይ የሚውለው የድጎማ ስምምነት ላይ የተካተቱትን የካውንቲውን ደንቦች እና ቅድመ ሁኔታዎች ላይ መስማማት።

## ፕሮፖዛሉን የማስረከቢያ ዝርዝሮች

ፕሮፖዛሎቹ በNotice of Funding Availability for Child Care Capacity Building & Quality Improvement ድር ጣቢያ ላይ ማስገባት ይችላል። **የፕሮፖዛሉ የማስረከቢያ የመጨረሻ ቀን አርብ፣ ዲሴምበር 20 ቀን፣ 2024 ዓ.ም 5:00 PM ሰዓት ድረስ ነው።**

ይሄንን NOFA በተመለከተ ከታች እንደተጠቀሰው የሚቀርቡ ጥያቄዎች እና የማብራሪያ ጥያቄዎች ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 2 ቀን፣ 2024 ዓ.ም እስከ 5:00 PM ሰዓት ድረስ ለኤልዛቤት ማትሎክ [Elizabeth Matlock] በኢሜይል አድራሻ ematlock@arlingtonva.us ላይ መቅረብ አለባቸው።

## የጊዜ ሰሌዳ እና አሸናፊውን አመልካች የመምረጥ ሂደት

**እሮብ፣ ኦክቶበር 30 ቀን፣ 2024 ዓ.ም** – NOFA ይበተናል

**ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 12 ቀን፣ 2024 ዓ.ም፣ እስከ 5:00 PM ድረስ** – NOFAን በተመለከተ በጽሁፍ የሚቀርቡ ጥያቄዎች/የማብራሪያ ጥያቄዎች የማስገቢያ የመጨረሻው ቀን። ጥያቄዎቹ ለኤልዛቤት ማትሎክ [Elizabeth Matlock] በኢሜይል አድራሻ ematlock@arlingtonva.us ላይ ማቅረብ ይችላል።

**ሐሙስ፣ ኖቬምበር 14 ቀን፣ 2024 ዓ.ም፣ ሰዓቱ ለወደፊቱ ይፋ ይሆናል** – NOFAን በተመለከተ እና ሌሎች አጠቃላይ የመረጃ ጥያቄዎችን በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ የቅድመ-ፕሮፖዛል መፃፍ የመረጃ መስጫ ክፍለ ጊዜ በኢንተርኔት በኩል ይከናወናል። የመረጃ ክፍለ ጊዜ ላይ እና በኢሜይል የቀረቡ ጥያቄዎች ላይ የተሰጡ ምላሾች ኦንላይን በድረገጹ ላይ ሰኞ፣ ኖቬምበር 18 ቀን፣ 2024 ዓ.ም እስከ 5:00 pm ድረስ ይሰቀላሉ።

**አርብ፣ ዲሴምበር 20 ቀን፣ 2024 ዓ.ም፣ እስከ 5:00 PM ሰዓት ድረስ** – ፕሮፖዛሉን የማስረከቢያ የመጨረሻው ቀን። *ፕሮፖዛሉን እንዴት እንደሚያስገቡ መረጃ ለማግኘት "ፕሮፖዛሉን የማስረከቢያ ዝርዝሮች" ይመልከቱ።*

**ፌብሩዋሪ 2024** ዓ.ም – ጊዜያዊ ፕሮጀክቶችን የመምረጥ ሂደት

**ፌብሩዋሪ - ማርች 2025 ዓ.ም** – የድጎማ ገንዘብ ስምምነት ላይ ድርድር ማድረግ (አስፈላጊ ከሆነ) እና በካውንቲው ቦርድ ስምምነቶችን ማጽደቅ።

## የምዘና መስፈርቶች

ፕሮፖዛሎች የሚገመገሙት የሚከተሉትን ነጥቦች በመጠቀም ነው። ውጤቱ እንዴት እንደሚሰላ የሚያሳይ መመሪያ በዚህ ማስታወቂያ መጨረሻ ላይ ተገልጿል።

| ምድብ | ነጥብ |
|---|---|
| ምላሽ አሰጣጥ | 15% |

| | |
|---|---|
| (የማመልከቻ ደብዳቤ፣ መግቢያ እና አባሪ የተደረጉ ደጋፊ ሰነዶች) | |
| ጥራት | 25% |
| ፕሮፖዛል | 40% |
| ፍትሃዊነት | 20% |

## የሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶች

ፕሮፖዛሉ ተቀባይነት አግኝቶ ያሸነፉ እንደሆነ፣ አገልግሎት ሰጪዎቹ በዓመት ሁለት ጊዜ የማይበልጥ የሂደት ሪፖርት ማቅረብ ይኖርባቸዋል። እነዚህ ሪፖርቶች ስለ ፕሮግራሙ ሂደት እና ስለ ገንዘብ አጠቃቀም ክፍል ሊኖራቸው ይገባል።

- የፕሮግራሙ ሂደት ሪፖርት፡- አገልግሎት ሰጪዎቹ የጥራት ደረጃ መሻሻልን የሚያሳዩ ማንኛውም ተዛማጅ መረጃዎችን እና ትርክቶችን ጨምሮ፣ የፕሮጀክቱን ሂደት ደረጃ ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል።
- የገንዘብ አጠቃቀም ሪፖርት፡- አገልግሎት ሰጪዎቹ ማስረጃ ሰነዶችን ጨምሮ (ልክ እንደ ኢንቮይስ ወይም ደረሰኞች ያሉትን) ያወጡት ወጪ ላይ ሪፖርት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

## ሌላ መረጃ

ካውንቲው ፕሮፖዛሉን ለህዝብ ክፍት አያደርግም።

ካውንቲው ማንኛውም ወይም ሁሉንም የቀረቡትን ፕሮፖዛሎች የመሰረዝ፣ ይሄንን ጥያቄ የመሰረዝ እና በቅደም ተከተሉ ውስጥ የሚገኙ ማንኛውም ኢመደበኛ ወይም ወጥ ያልሆኑ ነገሮችን የማንሳት መብቱ የተጠበቀ ነው።

አርሊንግተን ካውንቲ በሃይማኖት የተመሰረቱ ድርጅቶች ላይ አድሎ አይፈጽምም።

ካውንቲው ይሄ NOFA ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ያሉ አመልካቾችን እንደ አሸናፊ ሊመርጥ ይችላል፣ ይሄም የሚሆነው የሚሰጠው የገንዘብ አቅርቦት በዚህ NOFA ውስጥ ላይ የተቀመጡት ግቦች ጋር እንደሚሄዱ ካውንቲው ካረጋገጠ በኋላ ነው።

**የጥሩ ፕሮፖዛል አፃፃፍ መመሪያ**

| ምድብ | ጥሩ የሆነ ፕሮፖዛል በውስጥ የሚይዘው… | ትልቁ ነጥብ |
| --- | --- | --- |
| ምላሽ አሰጣጥ | • ሁሉንም የተጠየቁትን መረጃዎች እና ደጋፊ ሰነዶችን ያካትታል | 15 |
| ጥራት | • በርካታዎቹን የልጆች በጎነት ሁኔታዎች (አካላዊ፣ አእምሮዓዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ) ላይ ያካትታል<br>• በርካታ፣ የተነጠሉ የድርጊቶች እና የስልቶች ምሳሌዎች ያካታል<br>• ድርጊቶቹ እና ስልቶቹ ለልጆቹ ዕድሜ የሚመጥኑ ናቸው<br>• ድርጊቶቹ እና ስልቶቹ በግልጽ የልጆቹ በጎነት እና ዕድገት ጋር ይገናኛሉ | 25 |
| ፕሮፖዛል | • ፍላጎትን እና ፕሮጀክቱ የሚሸፍነውን የገበያ ፍላጎት በግልጽ ማብራሪያ ይሰጣል<br>• የሚሰጠው ገንዘብ እንዴት አገልግሎት ላይ እንደሚውል በግልጽ የሚያሳይ ምክንያታዊ እና ማብራሪያ የሚሰጥ በጀት ያካታል<br>• ምክንያታዊ የሆነ የጊዜ ሰሌዳ ይካትታል<br>• ያላቸው ከሆነ፣ ቀጣይ ወጪዎችን እንዴት እንደሚሸፈኑ የሚያሳይ ከእውነት ያልራቀ ዕቅድ። | 40 |
| ፍትሃዊነት | • ማንኛውም ተዛማጅ፣ ንጥል ታሪኮችን ወይም መረጃዎችን ጨምሮ ለልጆቹ እና ለቤተሰቦቻቸው ውስጥ ያሉትን ኢፍትሃዊነት ወይም ክፍተቶችን በፕሮጀክቱ ውጤት እንዴት መቀነስ እንደሚችሉ ማብራራት<br>• ከበርካታ ቡድኖች (ሰራተኞች፣ ልጆች፣ ቤተሰቦች) ጋር አካታችነትን ለማሳደግ ልዩ ተግባራትን እና ስልቶችን በግልጽ ማብራራት | 20 |